DISTRICT OF COLUMBIA PUBLIC SCHOOLS

ይህ የሁለተኛ-ደረጃ የደረጃ-አሰጣጥ እና ሪፖርት-ማድረጊያ ፖሊሲ (Secondary Grading and Reporting Policy)፣ ከዚህ ቀደም በዚህ ጉዳይ ላይ፣ በDCPS ታውጆ የነበረውን ሁሉንም ፖሊሲ፣ ሜሞራንዳ (memoranda)፣ እና/ወይም መመሪያ የሚሰርዝ እና የሚተካ ነው።

**ቻንስለሩ ያጸደቁት:** [signature]
**በስራ-ላይ የዋለበት ቀን:** ኦገስት (August) 26 ቀን 2024

# የሁለተኛ-ደረጃ የደረጃ-አሰጣጥ ሪፖርት-ማድረጊያ ፖሊሲ (Secondary Grading and Reporting Policy)

## I. ዓላማ እና የስፋት-መጠን

የኮሎምብያ ዲስትሪክት የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (The District of Columbia Public Schools (DCPS)፤ ተልዕኮ - ተማሪዎች - በሚያሳድጋቸው አካባቢ-ውስጥ - ጠንከር-ብለው በተሰጡ እና አስደሳች-በሆነ የትምህርት ተሞክሮዎች ውስጥ ሆነው፣ ወደ ሙሉ አቅማቸውን እንዲደርሱ ማድረግ ነው። DCPS፤ ለሁሉም የማንነት-መለያዎች እና የብቃት-ችሎታ - የተማሪዎች እድገትን በማፋጠን ላይ ያተኮረ ሲሆን፤ ይህም - ዕድል ለማግኘት እና በመማር ላይ-የሚገኙትን እንቅፋቶችን ለማስወገድ - ፍትሃዊ-በሆነ ሁኔታ ማግኘት-መቻላቸውን በማረጋገጥ ነው። ይህ ፖሊሲ፣ ለሁለተኛ-ደረጃ ተማሪዎች (ማለትም፤ ከ6 – 12 ክፍሎች) - በተማሪ የቀለም ትምህርት ሂደት ላይ፣ ለደረጃ-አሰጣጥ እና ሪፖርት-ማድረግ - የDCPS መስፈርቶች የሚያስተላልፍ-ነው።

DCPS፤ የውጤት-ደረጃዎች - ቀጣይነት-ባለው የትምህርት አገልግሎት ውስጥ የሚገኙ-መሆናቸን የሚያምን-ሲሆን፣ በተማሪው የትምህርት ቤት የስራ-መስክ ላይ ባደጉባቸው-ነገሮች ላይ እና በጎለበቱበት-ነገሮች ላይ በመዝገብነት በመያዝ-ላይ እያሉ፣ ወቅታዊ-የሆነ አስተያየትን ይሰጣሉ፣ እና የየግል የትምህርት-አሰጣጥ ዕቅድ ላይ እገዛ-ያደርጋል። በመሆኑም፣ የውጤት-ደረጃዎች (grades) - በDCPS ሥርዓተ-ትምህርት ላይ ተመስርተው የሚማሩ፣ የተማሩ እና የታዩ የይዘት የችሎታ እና የእውቀት ሁኔታ መለኪያዎች ናቸው፣ እና በሁሉም ትምህርት ቤቶች መካከል - በተቀመጡት መለኪያዎች ውስጥ፣ ግልጽ እና ወጥነት-ያላቸው ናቸው። የደረጃ-ውጤቶች (Grades)፤ በመደበኛዎች-ላይ መሠረት ያደረገ - በተማሪው መማር-ላይ ምስክር ሆኖ የተመሰረተ - የቤት/ክፍል ስራዎች (assignments)፣ እና በተርሙ/term ውስጥ-ሙሉ ባለው የክፍል-ስራዎች (assessments) ላይ - መሠረታዊነት ባለው የኮርስ ተሳትፎን በመሣየት ላይ መሠረት ያደረገ ነው። የደረጃ-ውጤቶች (Grades)፤ ተማሪዎችን - ለያይቶ-ለመመደብ፣ የዕድል ክፍተቶችን ለማስቀጠል ወይም የተማሪዎችን ባህሪይ ለመቆጣጠር - የሚያገለግሉ ዘዴዎች አይደሉም። የደረጃ-ውጤቶች (Grades)፤ በተቋም ተወዳዳሪነት ወይም-ደግሞ በተስማሚነት ላይ የተመሰረቱ አይደሉም፤ እንዲሁም-ደግሞ - ተጠያቂነትን ለማስተማር ወይም ለተማሪዎች ሊያስከትል የሚችለውን-ቅጣት ለማስተማር፣ የሚያገለግል-መሣሪያ አይደለም።

ይህ ፖሊሲ፣ ከዚህ ቀደም በዚህ በሚመለከተው ጉዳይ ላይ፣ በDCPS ታውጆ የነበረውን ሁሉንም ፖሊሲ፣ ሜሞራንዳ (memoranda)፣ እና መመሪያ የሚሰርዝ እና የሚተካ ነው።

## II. ሥልጣን እና በስራ-ላይ የሚውል ሕግ (AUTHORITY AND APPLICABLE LAW)[1]

| **ምንጭ/Source** | **ጥቅስ (Citation)** |
|---|---|
| የኮሎምብያ ዲስትሪክት ሕግ | D.C. Official Code § 38-781.01 *et seq.* – የተማሪ ወደሌላ ክፍል ማለፍ/Student Promotion |
| የኮሎምብያ ዲስትሪክት የማዘጋጃ ቤት ደንቦች | የስቴት የትምህርት የበላይ ተቆጣጣሪ ቢሮ (Office of State Superintendent of Education)<br>- 5-A DCMR Chapter 21 – አስገዳጅ-የሆነ ትምህርት እና በትምህርት ቤት የመገኘት (Compulsory Education and School Attendance) - 5-A DCMR § 2203 – የቀለም-ትምህርት መስፈርቶች/Academic Requirements [ለምርቃት]<br>- 5-A DCMR Chapter 24 – ጥምረት-ያለው የምዝገባ ደንቦች/Dual Enrollment Regulations<br>- 5-A DCMR § 2813 – [የሕዝብ-ትምህርት ቤቶች ያልሆኑ/Nonpublic School] የክፍል-ደረጃዎች እና ወደሌላ-ክፍል ማለፍ/Grades and Promotions<br><br>District of Columbia Public Schools - 5-B DCMR § 2103 – ያለማቋረጥ-መቅረት (Truancy)<br>- 5-B DCMR Chapter 22 – የክፍል-ደረጃዎች፣ ወደሌላ-ክፍል ማለፍ፣ እና ምርቃት/Grades, Promotion, and Graduation<br><br>ዋናው/ኦሪጅናል ታይትል (Original Title) 5<br>- 5-E DCMR Chapter 22 – የክፍል-ደረጃዎች፣ ወደሌላ-ክፍል ማለፍ፣ እና ምርቃት/Grades, Promotion, and Graduation - 5-E DCMR Chapter 26 – የተማሪ መዝገቦች/Student Records |

1 በዚህ ፖሊሲ ውስጥ ያለ ምንም-ነገር፣ የፌደራል፣ ስቴት፣ ወይም የአካባቢው (local) ሕግን የሚተካ አይሆንም።

## III. ቁልፍ-የሆኑ አባባሎች እና ትርጉሞች

**የላቀ ደረጃ ምደባ (Advanced Placement (AP)** ማለት፤ የኮሌጅ-ደረጃ ኮርሶች ሲሆኑ - የኮሌጅ ቦርድ መመሪያዎች (The College Board guidelines)ን እና የፈተና-አሰጣጥ ስር ዓትን የሚከተል-ነው።[2]

**የጥምረት ምዝገባ ፕሮግራም (Dual Enrollment Program)** ማለት፣ የከፍተኛ-ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች - በተፈቀደ የኮሌጅ ኮርሶች ውስጥ ተመዝግበው የሚማሩ እና ሁለቱንም የከፍተኛ-ደረጃ ትምህርት ቤት እና የኮሌጅ ክሬዲትን የሚያገኙ።[3]

**ፈቃድ-ያገኘ መቅረት (Excused Absence)** ማለት፣ ዕድሜው-ለትምህርት የደረሰ ተማሪ - እውቅና-ባለው ህጋዊ ምክንያት - ከ'ኮሎምቢያ ዲስትሪክት የማዘጋጃ-ቤት ደንቦች (District of Columbia Municipal Regulations (DCMR)' እና በ'DCPS የትምህርት-ገበታ ላይ መገኘት እና የመቅረት ፖሊሲ/*Attendance and Truancy Policy*'ን በተከተለ-ሁኔታ ከትምህርት-ቤት በሚቀር-ጊዜ ነው።[4]

**የውጤት-ደረጃ አማካኝ ነጥብ/Grade Point Average (GPA)** ማለት፤ በትምህርት-ዓመቱ ተርም (term) ወቅት ውስጥ፣ የተጠራቀመው የተማሪው ውጤቶች በአማካኝ/average ሆኖ - ማለት ነው።

**የከፍተኛ-ደረጃ ትምህርት ቤት የትምህርት-ማስረጃ/High School Transcript** ማለት፤ የኮሌጅ ዲፕሎማን ለማግኘት-በሚገፋበት ጊዜ፣ የኮርሶች፣ የክፍሎች እና የተማሪው GPA - ይፋዊ-የሆነ መዝገብ ነው።

**ኦነርስ/Honors** ማለት፤ በአንድ-ዓይነት የትምህርት ዓይነት ውስጥ - ከአጠቃላይ ኮርሶች ጥልቀት-ባለው ሁኔታ የሚሸፍኑ ኮርሶች - ነው።[5]

**ዓለም-አቀፋዊ ባካሎሪየት (International Baccalaureate (IB)** ማለት፤ የዓለም-አቀፍ ብካሎሪየት ድርጅት (International Baccalaureate Organization)ን መስፈርቶች የሚከተል የጥናት ፕሮግራም ነው።[6]

**ዘግይቶ መግባት (Late Entry)** ማለት፤ የትምህርት-አሰጣጥ ኮርሱ ከተጀመረ-በኋላ - 50% ካለፈ-በኋላ - ተማሪው በሚመዘገብ ጊዜ ነው።

**የባለብዙ-ቋንቋን የሚማሩ (Multilingual Learner)** ማለት፤ ለESOL (እንግሊዘኛ-ቋንቋ - ሌላ-ቋንቋዎችን ለሚናገሩ/English for Speakers of Other Languages) አገልግሎቶችን - እንደ ክፍል-ደረጃ ይዘን ለማግኘት-የሚያስችለው፤ ከዚህ-ቀደም እንደ እንግሊዘኛ-ቋንቋን የሚማሩ (English language learner) ተብሎ-ይታወቅ የነበረውን፤ ብቁነት ያላው ተማሪ።

**ወላጅ (Parent)** ማለት፤ የተፈጥሮ ወላጅ የሆነ፣ የማደጎ አሳዳጊ-ወላጅ/adoptive parent፣ የእንጀራ-ወላጅ/stepparent፣ ሌላ ቀደምት-የሆነ እንክብካቤ-ሰጪ፣ ወይም ሌላ ማንኛውም ሰው - ተማሪውን በህጋዊነት ለማሳደግ በፍርድ-ቤት ትዕዛዝ ያገኘ።[7]

**ፈቃድ-ያላገኘ መቅረት (Unexcused Absence)** ማለት፣ ዕድሜው-ለትምህርት የደረሰ ተማሪ - እውቅና-ያለው ህጋዊ ምክንያት ሳይኖረው - ከ'ኮሎምቢያ ዲስትሪክት የማዘጋጃ-ቤት ደንቦች (District of Columbia Municipal Regulations (DCMR)' እና በ'DCPS የትምህርት-ገበታ ላይ መገኘት እና የመቅረት ፖሊሲ/*Attendance and Truancy Policy*'ን[8] ባልተከተለ-ሁኔታ፤ የወላጅ ፈቃድ-ሳይኖረው - ከትምህርት-ቤት በሚቀር-ጊዜ ነው።[9]

---

2 5-B DCMR § 2200.7.
3 5-A DCMR § 2400.1.
4 *Available at* dcps.dc.gov/publication/attendance-and-truancy-policy.
5 5-B DCMR § 2200.7.
6 5-B DCMR § 2200.7.
7 *See* D.C. Official Code § 38-781.01(4).
8 *Available at* dcps.dc.gov/publication/attendance-and-truancy-policy.
9 *See* 5-A DCMR § 2102; *see also* 5-A DCMR § 2199.

## IV. መስፈርቶች

### A. የደረጃ-አሰጣጥ (Grading)

አስተማሪዎች፤ የተማሪውን ስራ ለመገምገም፣ ቀደምት-የሆነ ኃላፊነት አላቸው።[10]

ሁሉም ተማሪዎች፣ ባለሁለትቋንቋን የሚማሩ (Multilingual Learners (MLs)ን እና ከጉዳተኝነት (disabilities) ጋር የሚገኙ ተማሪዎችን ጨምሮ፣ የDCPS የይዘት መደበኛዎች/content standards ውጤታማነትን-ለማግኘት፣ የትምህርት-አሰጣጥ አመራርን ያገኛሉ።[11] MLs - የእንግሊዝኛ-ቋንቋ ችሎታን ለማዳበር እና የአካዳሚክ ይዘትን ለመቆጣጠር የሚያግዝ - ልዩ-የሆነ የትምህርት-አሰጣጥን ያገኛሉ። በይዘት-ዙሪያው ውስጥ - የተማሪ ውጤት፤ የተማሪውን የእንግሊዘኛ-ቋንቋ ችሎታ ማግኘቱን የሚያንጸባርቅ ሳይሆን፣ ነገር-ግን የይዘት መደበኛ-ደረጃዎች ላይ ውጤታማነትን-ያሳያል።[12] የየግል የትምህርት ፕሮግራም (Individualized Education Program (IEP) ተርሞች/teams ወይም የ'Section 504' ተርሞች/teams - ተገቢ-የሆኑ ማመቻቻዎችን እና የስርዓተ-ትምህርት ማስተካከያዎችን - በሚያስፈልጉበት ቦታ-ላይ የሚወስኑ-ናቸው። የተማሪ የውጤት-ደረጃ፣ ይህ ማመቻቻዎች/accommodations መደረጋቸውን የሚያንጸባርቁ-አይሆኑም።[13]

የክሬዲት መልሶ-ማነሳሻ (Credit Recovery) ኮርሶችን ጨምሮ - በማዕከላዊ አገልግሎቶች የጸደቀ - ብቃት-ተኮር ኮርሶች የሚሰጡ - ሁሉም ትምህርት ቤቶች፤ የኮርስ ውጤት እንዴት እንደሚወሰን ለተማሪዎች እና ቤተሰቦች - ከሚፈለገው ስሌት በተለየ መልኩ የሚወሰን ከሆነ - ከጽሁፍ-ማብራሪያዎች ጋር በSection IV.B (Term Grade Calculations) መስጠት አለባቸው። በእያንዳንዱ ኮርስ መጀመሪያ-ላይ ወይም በምዝገባው-ጊዜ፤ የጽሁፍ መግለጫዎች መቅረብ-አለባቸው።

1. የደረጃ-ውጤት - ማስገባት/Grade Entry

በሁለተኛ-ደረጃ ኮርሶች ውስጥ የሚገኙ አስተማሪዎች (ማለትም፣ ከ6 – 12 ክፍሎች) - ኮርሶቹ በሚገናኙበት - ለእያንዳንዱ አምስት (5) የትምህርት ቀናቶች - ቢያንስ ሁለት (2) የውጤት-ደረጃዎች/grades - መመዝገብ-አለባቸው።[14] አስተማሪዎች፣ ቀጣይነት-ያለው፣ ጊዜውን-የጠበቀ አስተያየትን ለተማሪዎች እና ወላጆች ለመስጠት፣ መስፈርቱን-መጠን ባሳደገ ሁኔታ እና በመደበኛነት ውጤት-የተሰጠውን ስራ እንዲመልሱ - ይበረታታሉ። አስተማሪዎች፤ ድብልቅ-የሆነ - ተማሪ ተሳትፎ፣ የተማሪ ልምምድ እና መተግበሪያን፣ እና የግምገማ የውጤት-ደረጃዎችን[15] - የተለያዩ አስተያየቶችን - በተርሙ (term) ውስጥ-ባለው ጊዜ ውስጥ፣ ለተማሪዎች እና ወላጆች ለመስጠት - እንዲመዘግቡ ይበረታታሉ።

በ'gradebook' ውስጥ፤ እንደየ-አስፈላጊነታቸው መሠረት፣ የ10፣ 20፣ 25፣ 50፣ ወይም 100 ነጥቦች ዋጋ ያላቸውን ነጥብ ሊሰጡ የሚችሉበት የቤት/የክፍል ስራ (assignments)፤ (ለምሳሌ፤ የቤት ስራ (assignment) ምናልባት የ10 ነቦችን ብቻ ሊያስገኝ ሲችል፣ በአንፃሩ ደግሞ ፈተናው 100 ነጥቦች ሊኖሩት ይችላል)። የ'ደረጃ-መዝገቦች (Gradebooks)'፣ የቤት/ክፍል ስራ (assignment) ውጤትን በጊዜው ለመመዝገብ እንዲቻል፣ ሣምንታዊ ቁጥጥር ይደረግበታል። ቢያንስ ዘጠኝ (9) የቤት/የክፍል ስራዎች (assignments) ለተርሙ (term) ካላስገቡ፤ አስተማሪዎች የተርሙን ደረጃ (term grade) ማስገባት አይፈቀድላቸውም።

አስተማሪዎች፤ ተማሪው ተገቢ-የሆነ ጥረትን ባሳየባቸው የቤት/ክፍል ስራዎች (assignments) - (ማለትም፤ ለተማሪው ላስገባው ነገር፣ ምላሽ፣ ጥረት ወይም ስራውን-ለማጠናቀቅ ላደረገው ጥረት ምስክር-የሚሆኑትን) በትምህርት ቤቱ የመመሪያ-መጽሐፉ/handbook ወይም በድህረ-ገጹ ላይ በቀረበው-መሠረት - አነስተኛ/minimum የውጤት-ደረጃ የሆነውን - "F"ን (በ63% የተሰላውን) - መድበው-መስጠት አለባቸው። ሁሉም የ"F" ውጤትን ያገኙ በቤት/ክፍል ስራዎች (assignments)፣ እንደ - ያልተጠናቀቀ (incomplete) መታየት ያለበት በመሆኑ፣ ተማሪው እንደገና በመስራት እና የቤት/የክፍል ስራውን (assignment) እንደገና ማስገባት ይችላል። ተማሪው በቤት/ክፍል ስራው (assignment) ላይ ካልሰራ ወይም ካላስገባ፤ በቤት/ክፍል ስራው (assignment) እንደ - የ"WS" (በ50% የተሰላ/calculated) ውጤት መስጠት አለበት።

---

10 5-B DCMR § 2200.4.
11 5-B DCMR § 2200.5.
12 5-B DCMR § 2200.5(a).
13 5-B DCMR § 2200.5(b).
14 ይህ መስፈርት፣ እንደ ወቅታዊ የደረጃ-አሰጣጥ እና የመዝገብ አያያዝ ልምዶች - ቀጣይነት-ባለው ሁኔታ ታስቦ-የተዘጋጀ ነው፣ እና ለA/B ኮርስ የጊዜ-ሰሌዳዎች የተቀመጡትን - የሚጠበቁ የሴሚስተር የጊዜ-ሰሌዳን ለማስፈጸም የሚጠበቅ-ሆኖ የተዘጋጅ ነው።
15 Section IV.B (Term Grade Calculations) ተመልከቱወይም የእነዚህን የውጤት ምድቦች መግለጫዎችን - መመልከት።

ተማሪዎች፤ ዋናውን ስራ ሲያስገቡ - ከላይ እንደተገለፀው ተገቢ-የሆነ ጥረት ካደረጉ፣ ማንኛውንም ደረጃውን ያልጠበቀ ስራ (ማለትም በ"D+" ወይም ከዚያ በታች የሆነ-ደረጃ ያለውን ስራ) ከልሰው-እንዲሰሩ - ዕድል ሊሰጣቸው ይገባል። አስተማሪዎች፤ ተማሪዎች ምደባዎችን በሚከልሱበት-ጊዜ፣ ማሻሻያዎቻቸውን ለመደገፍ የታለመ እና ተግባራዊ-የሆነ ምላሽ መስጠት ይጠበቅባቸዋል። ከዋናው/original መደበኛዎች ግምገማ ጋር ጎን-ለጎን ሆነው የሚሄዱ - አማራጭ-የሆኑ ግምገማዎች፤ በአስተማሪው ውሳኔ ሊሰጥበት የሚችል እና፣ አስተማሪዎች - በደረጃ-አሰጣጥ ደብተሩ (gradebook) ውስጥ፣ የተሻሻሉ ውጤቶችን ሲመዘግቡ መደበኛ የውጤት -አሰጣጥ ሂደቶችን እና የጊዜ-ሰሌዳዎችን መከተል አለባቸው። ሁሉም እንደገና-የገባው ስራ፣ ዘግይቶ-በማስገቢያው የጊዜ-ማብቂያው ቀን ላይ መግባት-አለበት፤ ይህም በዚህ-ላይ በተተረጎመው መሠረት ሲሆን፣ Section IV.C.6 (Makeup and Late Work)፤ እና - አንድ-ጊዜ ብቻ እንደገና-መግባት ይችላል። ከሚያስፈልጉ ሥርዓተ ትምህርት ተግባራት/Required Curricular Tasks በስተቀር፣ አንድ-ተማሪ ከለሳ-በተደረገበት ስራ ላይ -የሚያገኘው ከፍተኛ-የሆነ ውጤት/maximum grade - “C” ነው።

ሁሉም የሚያስፈልጉ ሥርዓተ ትምህርት ተግባራት/Required Curricular Tasks - ከ‘Canvas Course Companions’ ላይ - በዚህ-ክፍል/section ውስጥ በተገለጸው የጊዜ-ገደብ ማብቂያ መሠረት ክለሳ እና በድጋሚ-ማስገባት የሚቻል-ይሆናል። ሆኖም-ግን፤ ክለሳ-የተደረገበት ‘Required Curricular Tasks’ - የከፍተኛ-የሆነ ውጤት/maximum grade ገደብ የሌለው እና፣ በማንኛውም ውጤት እስከ “A” ድረስ ማግኘት-ይቻላል።

2. የደረጃ-አሰጣጥ መለኪያዎች (Grading Scales)

በሁለተኛ ደረጃ (ማለትም፤ ከ6 –12ኛ ክፍል) ከ“A” እስከ “F” ያሉት የውጤት-ደረጃዎች፤ በዚህ ፖሊሲ መሠረት በአስተማሪው ይመደባሉ - እና በእያንዳንዱ ኮርስ የይዘት-ደረጃዎች - ተማሪውን የውጤት-ደረጃ መጠኑን ያሳያል።[16] የመጨረሻ የደረጃ ውጤቶች/Final grades - የሁሉም የተርም/term የውጤት-ደረጃዎች አማካኝ-ውጤቶች የሆኑ-ሲሆን፣ ከመካከለኛ-ተርም/midterm ወይም ከመጨረሻ ፈተናዎች ሌላ ተጨማሪ ክብደት-ተሰጠበት የለም።[17]

የደረጃ-ውጤቶች/Grades፤ እንደሚከተሉት ይሆናሉ:[18]

[ሰንጠረዥ/table - በሚቀጥለው-ገጽ ላይ]

16 5-B DCMR §2200.7.
17 *See* 5-B DCMR § 2200.7.
18 *See* 5-B DCMR § 2200.7.

| ክፍሎች | የቁጥር አቻ/Numerical Equivalent | ክሬዲት/ Credit | GPA | Grade Point Value[19] | | | ተጨማሪ አስተያየቶች |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | On Grade (Unweighted) | Honors, Pre-AP | AP, IB, Dual Enrollment[20] | |
| A | ከ93% እስከ 100% | አዎን/Yes | አዎን/Yes | 4.0 | 4.5 | 5.0 | |
| A- | ከ90% እስከ 92% | አዎን/Yes | አዎን/Yes | 3.7 | 4.2 | 4.7 | |
| B+ | ከ87% እስከ 89% | አዎን/Yes | አዎን/Yes | 3.3 | 3.8 | 4.3 | |
| B | ከ83% እስከ 86% | አዎን/Yes | አዎን/Yes | 3.0 | 3.5 | 4.0 | |
| B- | ከ80% እስከ 82% | አዎን/Yes | አዎን/Yes | 2.7 | 3.2 | 3.7 | |
| C+ | ከ77% እስከ 79% | አዎን/Yes | አዎን/Yes | 2.3 | 2.8 | 3.3 | |
| C | ከ73% እስከ 76% | አዎን/Yes | አዎን/Yes | 2.0 | 2.5 | 3.0 | |
| C- | ከ70% እስከ 72% | አዎን/Yes | አዎን/Yes | 1.7 | 2.2 | 2.7 | |
| D+ | ከ67% እስከ 69% | አዎን/Yes | አዎን/Yes | 1.3 | 1.8 | 2.3 | |
| D | ከ64% እስከ 66% | አዎን/Yes | አዎን/Yes | 1.0 | 1.5 | 2.0 | |
| F | 63%[21] | የለም/No | አዎን/Yes | | | | |
| W | ለቅቆ-የወጣ | የለም/No | የለም/No | | | | |
| L | ዘግይቶ የገባ/Late entry | የለም/No | የለም/No | | | | ወደ AUD (ኦዲት/Audit) በሚከተለው ተርም/term መጨረሻ-ላይ - የኮርስ-ስራው ካልተጠናቀቀ፣ ተለውጦ-የሚገባ (Convert የሚሆን)። |
| I | ያልተጠናቀቀ (Incomplete) | የለም/No | የለም/No | | | | የኮርስ-ስራው ከ10 የትምህርት ቀናት በኋላ ካልተጠናቀቀ፣ ወደ 'F' የሚለወጥ |
| M | ህክምና | የለም/No | የለም/No | | | | |
| P | አልፏል (Pass) | አዎን/Yes | የለም/No | | | | |
| AUD | ኦዲት (Audit) | የለም/No | የለም/No | | | | |
| S | አጥጋቢ-የሆነ/Satisfactory | የለም/No | የለም/No | | | | በመማሪያ-ክፍል ወይም በሌላ የቀለም-ትምህርት ጊዜ ባልሆነ ላይ - ጥቅም-ላይ የሚውል |
| U | አጥጋቢ-ያልሆነ/ Unsatisfactory | የለም/No | የለም/No | | | | በመማሪያ-ክፍል ወይም በሌላ የቀለም-ትምህርት ጊዜ ባልሆነ ላይ - ጥቅም-ላይ የሚውል |
| WS[22] | ለማስገባት እየጠበቀ-የሚገኝ/Waiting for Submission | የለም/No | አዎን/Yes | | | | የቤት-ስራዎች/assignments ማስታወሻዎች - ገና-ያልገቡ/not yet been submitted። በ50% የተሰላ። |

19 የከፍተኛ-ደረጃ ትምህርት ቤት የውጤት ነጥብ አማካኞች/point averagesን ለማስላት - ተጨማሪ መረጃን ለማግኘት፣ እባካችሁ በ dcps.dc.gov/publication/calculating-high-school-grade-point-averages. ላይ ተመልከቱ

20 *See* 5-A DCMR § 2403.3.

21 DCPS - የውጤት-ደረጃ "F"ን - በ63% ያሰላል።

22 የ"WS" ማርክ/mark፣ ስራው ከገባ-በኋላ - ለመተካት እንደ ጊዜያ-የሆነ የውጤት-ደረጃ ሆኖ የታሰበ ነው።

የኮርሶች ውስጥ - በውጤት-ደረጃዎች የወደቁ እና ከመዋለሕፃናት እስከ አስራ ሁለተኛ (12) በውጤት-ደረጃዎች ለክሬዲት እንደገና-የተወሰዱ፤ ለማንኛውም ኮርስ ከዚህ-ቀደም ለተገኙ ውጤቶች መተኪያ-የሚሆኑ አይደሉም፤ ነገር-ግን በተማሪው የተጠራቀመው 'Grade Point Average (GPA)' ውስጥ ይካተታሉ።[23] እንደ የበጋ ትምህርት/Summer Learning፣ 'STAY' ትምህርት ቤት፣ ኦፖርቹኒቲ አካዳሚ/Opportunity Academy እና የምሽት ክሬዲት መልሶ-ማካካሻ ኮርሶች/Evening Credit Recovery courses - ባሉት-ውስጥ፣ በተራዘሙ የትምህርት ፕሮግራሞች ውስጥ - የተገኙ ውጤት-ደረጃዎች፣ እንደ መደበኛ ዓመት ኮርሶች - ተመሳሳይ የ'ክሬዲት' እና የ'GPA' የዋጋ-መጠን/value አላቸው።[24]

### B. የተርም/Term የውጤት-አሰጣጥ ስሌትን-ማስላት/Grade Calculations

የተርም የውጤት-አሰጣጦች/Term grades[25] የተማሪውን ስራ - ስብጥር-ባለው ሁኔታው ላይ ማንጸባረቅ ያለበት እና፣ የሚከተሉትን ምድቦች እና ክብደት-ማንሻዎችን በመጠቀም የሚሰላ-ነው: 10% የተማሪ ተሣትፎ/Student Engagement, 50% የተማሪ ልምምድ እና መተግበሪያ/Student Practice & Application፣ እና 40% ግምገማ/Assessment። ሁሉም ምድቦች፤ በተርሙ/term መጨረሻ-ላይ - በርካታ ግምገማዎችን መመዝገብ አለባቸው።

ምድቦች እና የክብደት-መጠናቸው/Categories and weights፤ በአስተማሪው የውጤት-መስጫ ደብተሮች ላይ ቀድሞው-የሚታዩ እና እንደሚከተሉት ተተርጉመዋል:

- **የተማሪ ተሣትፎ/Student Engagement (10%)**: ይህ ምድብ፤ የተማሪዎችን ሥራ የሚያቀርቡ፣ ሥራ የሚከለሱ፣ ወይም ሳምንታዊ የሥራ ዕቅዶችን ጊዜያቸውን እና ተግባራቸውን ለማከናወን እና የሥራ እቅዶቻቸውን በማጠናቀቅ - በትምህርት ቤት ውስጥ ንቁ ተሳትፎን ማሳየትን ያጠቃልላል። የሥራ ዕቅዶች፤ የየግል-የሆነ ክለሳ-ማድረግን ወይም የስራ-ማራዘሚያን - እንደየአስፈላጊነቱ ማድረግን - ሊያካትት ይችላል። በተጨማሪም፣ በክፍል ውይይቶች ወይም በቡድን እንቅስቃሴዎች ለማዳመጥ፣ የመናገር፣ የመጻፍ፣ የእርስ-በርስ ግንኙነትን የማድረግ ወይም የመምራት አቅም-እንዳላቸው በምስክርነት-ማቅረብን - በዚህ ምድብ ውስጥ ይካተታል። ተሣትፎ፤ በተማሪው የመማር-ሂደት ውስጥ አስተዋጽዖ ያደርጋል። መቅረቶች (Absences)፤ በተማሪ የተሣትፎ የውጤት-ደረጃ/Student Engagement grade ላይ በተቃራኒ-ሆኖ የሚቆጠር አይሆንም።

- **የተማሪ ልምምድ & ተግባር/Student Practice & Application (50%)**: ይህ ምድብ፤ በክፍል ውስጥ ከየየግል ትምህርቶች-የተገኙ ልዩ-የሆኑ እና የድምር ችሎታዎችን - የሚለማመዱ እና የሚተገበሩ፣ ሁሉንም የተማሪ የስራ ውጤቶች/work productsን - ያካትታል። የቤት/ክፍል ስራዎች (Assignments)፤ ተማሪዎች ያላቸውን ችሎታ በስኬታማነት እንዲያጣምሩ የሚያደግርላቸው እና በመተግበሪያ እና ልምምድ አማካኝነት ይዘትን እንዲያገኙ ያደርጋል። ወደ-የሚያስፈልጉ ሥርዓተ ትምህርት ተግባራት/Required Curricular Tasks - ከ'Canvas Course Companions' ላይ - የሚያደረጉ የስራ አመራሮች (Tasks leading)፤ የቤት/ክፍል ስራዎች/assignments ን በዚህ ምድብ ውስጥ አካተዋል። ተማሪዎች፤ በእነዚህ ስራዎች/tasks ላይ - ያላቸውን ብቃት ካላሳዩ፤ ስራዎቹን ለመከለስ፣ ውጤት-ደረጃውን ለማሳደግ እና የላቀ-ብቃትን ለማሳየት - የተለየ የጥራት ግብረመልስ (specific qualitative feedback)ን ያገኛሉ። በዚህ ዙሪያ-ያለው - ሥራ፤ በኮርስ ክፍሉ ውስጥ ውስብስብነት መጨመር ያለበት-ሲሆን፣ ይህም ወደ ድምር ግምገማዎች/cumulative assessments - ይዳብራሉ። እነዚህ ግምገማዎች በክፍል-ውስጥ ወይም ከክፍል-ውጪ የሚጠናቀቁ-ናቸው፣ እና በአስተማሪዎች፣ በእኩዮቻቸው፣ ወይም በመረጃ-ምንጮች - ሊደገፉ-ይችላሉ።

- **ግምገማ/Assessment (40%)**: ይህ ምድብ፤ ሁሉንም መደበኛ ግምገማዎች - ለእያንዳንዱ የተማሪ ችሎታዎች፣ እውቀት፣ የእድገት-ሂደት፣ እና የላቀ-ደረጃ - የሚያካትት-ይሆናል። በካንቫስ (Canvas) የኮርስ በራስ--የተመራ ለፈተኛ ዝግጅት (Course Companions) ውስጥ - በሚፈለጉት የስርዓተ-ትምህርት ስራዎች ውስጥ የተደረጉ ግምገማዎች - ይህም በዚህ ምድብ ውስጥ የተካተቱት - የተለመዱት-ዓይነት ፈተናዎች እና ጥያቄዎች/quizzes - እስከ በአፈጻጸም-ላይ መሠረት ያደረጉ ስራዎች፣ የተማሪን ችሎታ እና የአንድን አጠቃላይ ክፍል/unitን - እውቀት ያሳያሉ። ግምገማዎች የሚጠናቀቁት፣ በተናጥል በተወሰነ ጊዜ-ውስጥ በመደበኛ የፈተና አካባቢ ውስጥ እና የተማሪ ማመቻቻዎች (accommodations)ን በማክበር - ይጠናቀቃሉ። በDCPS ወይም በአስተማሪዎች - የሚከናወንኑ ይሆናሉ። በግምገማዎች ላይ ብቃታቸውን ያላሳዩ ተማሪዎች፣ በክለሳ ላይ የተለየ የጥራት ግብረመልስ (specific qualitative feedback) ያገኛሉ እና፣ ግምገማውን በመከለስ ወይም እንደገና በመውሰድ - በSection A.1 (Grade Entry) ላይ በተሰጠው-መሠረት፣ ውጤቱን ከፍ-ለማድረግ እና የላቀ ብቃትን ለማሳየት ይችላሉ።

---

23 5-B DCMR § 2200.8

24 5-B DCMR § 2200.8.

25 DCPS፣ የቀለም-ትምህርት የቀን-መቁጠሪያውን በአራት ተርሞች ይከፍላል፤ እያንዳንዱ ወደእኩል-የሚጠጋ ቁጥር-ያላቸውን የትምህርት ቀናት ይዘዋል። የ"advisory" ወቅት/period፤ በDCMR ላይ በተጠቀሰው-መሠረት - ከDCPS "term" ጋር-ተመጣጣኝ (equivalent የሆነ) ነው።

### C. የተማሪ የእድገት-ሂደትን - ሪፖርት-ማድረግ እና እርዳታ-መስጠት

#### 1. ማስታወቂያ/Notification

ተማሪዎች የይዘት መደበኛዎች (content standards)ን በማሳካት ረገድ ስላደረጉት እድገት፣ ወላጆች እና ተማሪዎች - በጽሁፍ እና በመደበኛነት መረጃ-ይደርሳቸዋል።[26] በዚህም-ሁኔታ፣ ርዕሰ መምህራኖች - ስለልጆቻቸው የቀለም-ትምህርት ሁኔታ፣ ማህበራዊ ወይም የባህሪይ እድገት ላይ ተጽእኖ ስላሳደረባቸው-ጉዳዮች - ማነጋገር የሚገባቸውን የትምህርት ቤት ሠራተኛ ስም እና የሚገኙበትን-አድራሻ፣ በሴፕቴምበር (September) ወር መጨረሻ - ላይ ስልክ-በመደወል - ወላጆች እንዲያውቁት-መደረጉን - የማረጋገጥ ኃላፊነት አለባቸው። የተማሪውን የእድገት ሂደት - ለባለብዙ-ቋንቋ ተናጋሪዎች (Multilingual learners) ግምገማ-በሚደረግበት ጊዜ፤ የይዘት የላቀ የብቃት-ደረጃ (content mastery) እና የ'WIDA English Language Development Standards' ጥቅም-ላይ መዋል አለባቸው። የተማሪዎችን - ቋንቋን-የመጠቀም አቅም (productive language) ላይ ግምገማ በሚደረግበት ጊዜ፤ የ 'WIDA Speaking and Writing Rubrics' - ከ'content rubric' ጋር-ጎን ለጎን ሆኖ ጥቅም-ላይ መዋል አለበት።

#### 2. የዕድገት-ሂደት (Progress) ሪፖርቶች

የዕድገት-ሂደት (Progress) ሪፖርቶች፣ በእያንዳንዱ ተርም/term አጋማሽ-ነጥብ ላይ - ለሁሉም ተማሪዎች የሚሰጡ-ናቸው። የይዘት-መደበኛው (content standard) ላይ ውጤታማ-ሆኖ ለመድረስ ባለው ሂደት-ላይ የሚገኘውን ማንኛውንም ለውጥ ለማመልከት፣ ወይም ተማሪዎች አጥጋቢ-ሆኖ ያሳዩትን ዕድገታቸውን እንዲቀጥሉበት ለማበረታታት፤ አስተማሪዎች፣ በዕድገት-ሂደት ሪፖርቱ ላይ - የውጤት-ደረጃዎችን እና አስተያየቶችን - መስጠት አለባቸው። የአስተማሪ አስተያየቶች - "C" ወይም ከዚያ-በታች ላገኙ ተማሪዎች - የሚያስፈልጉ ናቸው። አስተያየቶቹ፤ በተለየ-ሁኔታ - ተማሪው ለምን-እየታገለ እንደሆነ ወይም እንደወደቀ እና፣ በክፍሉ ውስጥ በዕድገት-እየተራመዱ ለማለፍ ወይም ለማሻሻል ምን-ማድረግ እንዳለባቸው በግልጽ-ማብራራት አለባቸው። ወላጆች - የሚመርጡት ግንኙነት-የማድረጊያ ቋንቋቸው - ከእንግሊዝኛ-ቋንቋ ሌላ መሆኑን ያመለከቱ-ከሆነ፤ የተተረጎመውን - ሰነድ እንዲያገኙ መደረግ ያለበት ወይም የሰነዱን ትክክለኛ-የሆነውን ማብራሪያ በስልክ-የማስተርጎም አገልግሎት/ telephonic interpretation አማካኝነት - (ለምሳሌ፤ በቋንቋ-እርዳታ ማግኛ መስመር/Language Line) ማግኘት አለባቸው።[27]

ሁሉም ተማሪዎች፣ ምንም-እንኳን የእድገት-ሂደት ሪፖርታቸውን በሚቀበሉበት ጊዜ - የወደቁ-ቢሆንም እንኳን፤ የእድገት-ሂደት ሪፖርቶች ከተሰጡ-በኋላ፣ ስኬታማነትን ለማሳየት እድል ሊሰጣቸው ይገባል። ተገቢ-የሆነው ጣልቃ-ገብነቶችን ለመለየት፤ አስተማሪዎች - ከተመደቡት ሠራተኞች፣ የተማሪው ወላጅ(ጆች)፣ እና ከተማሪው-ጋር - መስራት አለባቸው።

#### 3. ሪፖርት ካርዶች

ለሁለተኛ-ደረጃ ትምህርት ቤቶች - ሪፖርት ካርዶች፣ በእያንዳንዱ ተርም/term መጨረሻ ላይ የሚሰጡ እና የተማሪውን የመጨረሻ ተርም የውጤት-ደረጃን - ለእያንዳንዱ ክፍል የሚያካትት-ይሆናል። የሪፖርት ካርዶች፤ የተርሙ (term) ጊዜ-ካለቀ በኋላ፣ ከአስራ ሁለት (12) የትምህርት ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ይከፋፈላል።[28]

#### 4. የወላጅ-አስተማሪ ኮንፈረንሶች

የወላጅ-አስተማሪ ኮንፈረንሶች - በተማሪው ወላጅ እና ተማሪው ተመዝግቦ በሚማርበት ውስጥ፤ በክፍል፣ ኮርስ፣ እና የትምህርት-ዓይነት አስተማሪው ጋር - በሁለቱ-መካከል የሚደረግ የጊዜ-ሰሌዳ የተያዘላቸው ስብሰባዎች ናቸው። በእነዚህ ኮንፈረንሶች ላይ ተማሪውን ማካተት-ተመራጭ የሆነ ልምድ-ነው። እነዚህ ስብሰባዎች ወይም ኮንፈረንሶች - ለወላጅ እና ለተማሪ - ስለተማሪው የእድገት ሂደት መረጃ-እንዲያገኙ እና ቡድኑ ስለ ስልቶች፣ እርዳታዎች፣ እና የተማሪውን ውጤታማነት ለማቀድ - ውይይቶችን ለማድረግ የተቀረጹ-ናቸው። በኮንፈረንሱ-ላይ ውይይት-ሊደረግባቸው የሚችሉ ርዕሶች - የቀለም-ትምህርት፣ በትምህርት-ገበታ ላይ መገኘት እና ባህሪይ ያሉትን-ሊያካትት ይችላል። የወላጅ-አስተማሪ ኮንፈረንሶች፤ በተርሙ/term "F" ላገኙ ተማሪዎች - ሪፖርት ካርዱ ተከፋፍሎ-በተሰጠበት በሁለት (2) ሣምንታት ውስጥ መካሄድ-አለበት። ተማሪው - በበርካታ ትምህርቶች "F" ካገኘ፤ በእነዚህ ክፍሎች ውስጥ የሚገኙ አስተማሪዎች - የጋራ-ኮንፈረንስን ከወላጅ(ጆች ጋር ሊያደርጉ ይችሉ-ይሆናል።

---

[26] *See* 5-B DCMR § 2200.9.

[27] ስለ በቋንቋ እገዛ ማግኘት/language access መስፈርቶች ተጨማሪ መረጃን ለማግኘት፣ እባካችሁ የ*'Language Access Policy'*ን እዚህ ተመልከቱ dcps.dc.gov/page/language-access-policy.

[28] 5-B DCMR § 2200.10.

5. እየወደቁ-ባሉበት የውጤት-ደረጃ ላይ - ለሚገኙ ተማሪዎች የሚሰጡ-እርዳታዎች

በተርሙ/term አጋማሽ-ነጥብ ላይ፤ ተማሪው በመውደቁ አደጋ-ላይ የሚገኝ-ነው በሚል አስተማሪው የሚያስቡ-ከሆነ እና አስፈላጊ-ሆኖ የሚገኝ-ከሆነ - ተማሪውን - ወደ የተማሪ እርዳታ ሰጪ ቡድን (Student Support Team (SST) ለመምራት (refer ለማድረግ)፤ አስተማሪዎች - ለወላጆች በጽሁፍ ማሳወቅ አለባቸው።[29] ከዚያም-በመቀጠል - በውጤት-ደረጃቸው እየወደቁ ለሚገኙ ተማሪዎች - የትምህርት-አሰጣጥ እርዳታ ዕቅድ መቀረጽ-አለበት። እነዚህ ዕቅዶች - እያንዳንዱ ተማሪ ውጤታቸውን-ለማሻሻል የሚያስፈልገውን-ነገር - መለየት ማስቻል-አለበት። ከ'IEP' ጋር የሚገኙ፣ ተማሪዎች ወይም 'Section 504 plan' ያላቸው፤ የእርዳታ-መስጫ ዕቅድ (support plan) - ሊኖራቸውም-ይችላል። የትምህርት-አሰጣጥ እርዳታ ዕቅዶች - በጊዜ-መጠናቸው እና የአሰጣጥ-ጥንካሬአቸው የሚለያዩ-እና፣ አሁን-ካለው የትምህርት ቤት ልምዶች፣ የጣልቃ-ገብነት እቅድ-አወጣጥ፣ እና የተማሪ እርዳታ-ሰጪ ቡድን (Student Support Team (SST) ሂደት-ጋር ጎን-ለጎን ሆኖ የሚሄዱ መሆን አለባቸው።[30]

ሁሉም ዕቅዶች በአስተማሪዎች ተመዝግበው የሚጸድቁ ሆነው-እያሉ፣ ተማሪዎች - የራሳቸውን ዕቅድ ለማውጣት እንዲረዷቸው ዕድል-ቢሰጣቸው፣ የተሻለው አሠራር ነው። አስተማሪዎች፤ የተደረጉትን ሁሉንም ጥረቶች - ከተማሪ እና ከወላጅ ጋር ግንኙነት-በማድረግ ስለ ዕቅዱ ለማሳወቅ፣ የጽሁፍ-ሰነዶችን መመያዝ-ማስቀመጥም አለባቸው። የዕቅዶቹ ቅጂዎች/Copies - ለተማሪው-ወላጅ(ጆች) መሰጠት ያለበት እና፣ በተማሪው ፋይል ውስጥም መቀመጥ-አለበት።

እያንዳንዱ አዋቂ (adult) ተማሪ፣ ወይም ለአካለ-መጠን ያልደረሰ (minor) ተማሪ -ወላጅ፤ የተማሪው ወደሌላ-ክፍል ማለፍ ወይም የምርቃት ሁኔታ - በሶስተኛ-ተርም/term አልቆ-ከተዘጋ በኋላ - አስራ-ሁለት (12) የትምህርት ቀናት ሳይልፍ፤ በጽሁፍ እንዲያውቁት ይደረጋል።[31] የዕድገት-ሂደት ሪፖርቶች (Progress reports) እና ሪፖርት ካርዶች (report cards) - ይህን መረጃ ለማጋራት ጥቅም-ላይ ይውላሉ፣ እና የተማሪው ወደሌላ-ክፍል ማለፍ ወይም የምርቃት ሁኔታን - ለተማሪዎች እና ለወላጆች ያሳውቃል። የኮርስ ወይም የውጤት-ደረጃን - መደበኛዎቹ/standardsን ያላሟላ ማንኛውም ተማሪ፣ በበጋ መማሪያ (summer learning) ውስጥ - ጊዜው-ሳያልፍ መመዝገብን ለማረጋገጥ - የመጨረሻው የትምህርት ቀን - ከማለፉ-በፊት፣ እንዲያውቁት-ይደረጋል።[32]

6. የማካካሻ-ጊዜ እና የዘገየ ስራ/Makeup and Late Work

ተማሪው፤ ከክፍል-ውስጥ ሳይገኝ-ቀርቶ በነበረበት ሁኔታ ላይ ያመለጠውን - አስተማሪዎች - ስራቸውን እንዲያካክሱ ዕድል እንዲያገኙ መስጠት ያለባቸው እና ዘግይቶ-የሚገባ ስራ (late work)ን መቀበል-ያለባቸው እና የውጤት-ደረጃ መስጠት-አለባቸው። በዕድገት-ሂደት ሪፖርቶች ከመሰራቱ በፊት-ማለቅና መግባት ያለባቸው ሁሉም - ለቤት/ክፍል ስራዎች (assignments) ዘግይቶ-የሚገባ ስራ (late work)፤ ከዕድገት-ሂደት ሪፖርት ማድረጊያ ወቅቱ ካለቀ-በኋላ መግባት-አለባቸው። ከዚህ የጊዜ-ወቅት በፊት መግባት-ያለባቸው - የቤት/ክፍል ስራዎች (assignments)፣ ከዚህ የጊዜ-ገደብ ማብቂያ በኋላ ተቀባይነት አይኖራቸውም። ከዕድገት-ሂደት ሪፖርት ማድረጊያው ወቅት ካለቀ-በኋላ የሚመደቡ - ሁሉም ለቤት/ክፍል ስራዎች (assignments) - ዘግይቶ-የሚገባ ስራ (late work)፤ በተርሙ/term መጨረሻ-ላይ የመግቢያ-ጊዜያቸው ይሆናል። አስተማሪዎች፤ ለእያንዳንዱ ተርም/term - የዕድገት-ሂደት ሪፖርት ማደረጊያው የጊዜ-ወቅት የሚያልቅበትን ቀን - ከተማሪዎች ጋር ግንኙነት-በማድረግ ያሳውቃሉ።

የቤት/ክፍል ስራዎች (assignments)ን በሰዓቱ-ማቅረብ እና ግባብነት-ያለው በትምህርት-ገበታ መገኘት (attendance)ን ለማበረታታት፣ ፈቃድ-ያላገኘ ከትምህርት-ገበታ መቅረቶች (unexcused absence)ን ተከትሎ - ዘግይተው-ለገቡ ስራዎች የሚሰጠው የውጤት ደረጃ - በአንድ (1) የፊደል ደረጃ/letter grade ይቀንሳል (ለምሳሌ፤ "A-" የነበረው - ወደ "B-" ይለወጣል)። ፈቃድ-ያገኘ መቅረቶች (excused absences) ያሏቸው-ተማሪዎች፤ ሙሉ ክሬዲት እንዲያገኙ እድል ሊሰጣቸው የሚገባ እና፣ ሳይማሩ-ያመለጣቸውን ስራ ለማጠናቀቅ ተመጣጣኝ ጊዜ ይሰጣቸዋል (ማለትም፤ ለእያንዳንዱ ያመለጣቸው ቀን - ከአንድ (1) ያላነሰ ተጨማሪ የቀን-መቁጠሪያ ቀን) ሁሉም የቤት/ክፍል ስራዎች (assignments) ተጓዳኝ-ሆኖ በተሰጣቸው የጊዜ-ገደብ ማብቂያዎች አኳይ የሚገቡ-ይሆናል። ካልሆነ-ግን፣ የውጤት-አሰጣጥ ማካካሻ ስራ በሚሰጡበት-ጊዜ ደረጃውን የጠበቀ-መልኩ፣ አስተማሪዎች - የውጤት አሰጣጥ ሂደቶችን - መከተል አለባቸው። በአስተማሪው ውሳኔ-መሠረት - አማራጭ የሆነ የቤት/ክፍል ስራዎች (Alternative assignments) ሊሰጡ-የሚችሉ እና መደበኛዎች (standards) - ከዋናው/ኦሪጂናል - የቤት/ክፍል ስራ (assignment) ጋር ጎን-ለጎን ሆኖ መሄድ-አለበት። ስለ ትምህርት-ቤት አቀፍ የማካካሻ ስራ ፖሊሲ (school-wide makeup work policy) በተመለከተ፣ በኮርሱ-መጀመሪያ ላይ - አስተማሪዎች የጽሁፍ ግንኙነት-ማድረጊያ/written communication ለተማሪው-መስጠት አለባቸው።

**D. የቀለም-ትምህርት ታማኝነት/Academic Integrity**

ትምህርት ቤቶች - ለተማሪዎች - የሚማሩበት እና ዕድገት-የሚያሳዩበት ወሳኝ-የሆነ ቦታ ሲሆን፤ በዚህም ቦታ ውስጥ - በቀለም-ትምህርት አካሄድ

---

[29] 5-B DCMR § 2200.9(b).
[30] በSSTs - ላይ ተጨማሪ መረጃዎችን ለማግኘት - እባካችሁ እዚህ ተመልከቱ dcps.dc.gov/page/student-support-teams. [31] 5-B DCMR § 2204.1.
[32] 5-B DCMR § 2200.11.

የሚያድጉበት፣ ወደ የወደፊት-ሕይወታቸው እና የስራ-መስካቸው የሚሰናዱበት፤ እና እንደ ጽናት፣ ችግሮችን-መፍታት፣ ፍትሃዊ-መሆን እና ታማኝነት - ባሉት ላይ - ጠቃሚ-የሆኑ የግል የማንነት-ባህሪያቶችን የሚያጎለብቱበት-ቦታ ነው። ማጭበርበር፣ ሌላ-የሰራውን ስራ-እራስ እንደሰሩ አስመስሎ ማቅረብ (plagiarism) እና ሌሎች የቀለም-ትምህርትን - የታማኝነት መርሆዎች ላይ ጥሰትን የሚያስከትሉ - ለትምህርት ቤቱን አካባቢ ስጋት-የሚፈጥሩ ድርጊቶች፤ በDCPS የተከለከሉ ናቸው።

የቀለም-ትምህርትን - የታማኝነት መርሆዎች መጣስ፤ አንድ ተማሪ የራሱን ስራ በማይሰራበት-ጊዜ ወይም በአስተማሪዎቹ በተደነገገው መመሪያ መሠረት ስራዎችን ሳያጠናቅቅ ሲቀር-ነው። ለቀለም-ትምህርት ታማኝነት ጥሰቶች - ትምህርት ቤቶች፣ በሚከተሉትን ጣልቃ-ገብነቶች እና ቅጣት-ሊያስከትሉ በሚችሉ ነገሮች ላይ መሠረት አድርጎ - እንደየ ጣፋቱ ደረጃ እና ተደጋጋሚነት - ምላሽ-ይሰጣል:

| | | ከተማሪው ጋር - 'Documented Notification' ማጋራት | ከወላጅ/አሳዳጊ ጋር - በሰነድነት-የተያዙ ስብሰባን ማካሄድ | በተማሪ ባህሪይ መከታተያ (Student Behavior Tracker (SBT) ውስጥ እና በፓኖራማ (Panorama) ውስጥ መግባት/Log in ማድረግ[33] | የመጀመሪያው የቤት/ክፍል ስራ የውጤት-ደረጃ/ Initial Assignment Grade | በድጋሚ-ማስገባት/ Resubmission |
|---|---|---|---|---|---|---|
| **አነስተኛ-የሆነ ጥፋትMinor Offense** | **የመጀመሪያ-ጥፋት/1st offense** | አዎን/Yes | በአማራጭነት-የሚደረግ (Optional) | በአማራጭነት-የሚደረግ (Optional) | እንደ "F" ሆኖ የውጤት-ደረጃ የተሰጠው | ለሙሉ ክሬዲት - አንድ ዳግም-ማስገባት፣ ተፈቅዷል |
| | **ሁለተኛ-ጥፋት/2nd offense** | አዎን/Yes | አዎን/Yes | በአማራጭነት-የሚደረግ (Optional) | እንደ "F" ሆኖ የውጤት-ደረጃ የተሰጠው | አንድ በድጋሚ-ማስገባት - ከአንድ የውጤት-ደረጃ ቅነሻ-ጋር የሚፈቀድ-ይሆናል |
| | **ሦስተኛ ጥፋት/3rd offense ወይም ከዚያ በላይ** | አዎን/Yes | አዎን/Yes | በአማራጭነት-የሚደረግ (Optional) | እንደ "F" ሆኖ የውጤት-ደረጃ የተሰጠው | ምንም ዳግም-ማስገባ/resubmission አልተፈቀደም |
| **ከፍተኛ-የሆነ ጥፋት/Major Offense** | **የመጀመሪያ-ጥፋት/1st offense** | አዎን/Yes | አዎን/Yes | አዎን/Yes | እንደ "F" ሆኖ የውጤት-ደረጃ የተሰጠው | አንድ በድጋሚ-ማስገባት - ከአንድ የውጤት-ደረጃ ቅነሻ-ጋር የሚፈቀድ-ይሆናል |
| | **ሁለተኛ ጥፋት/2nd offense ወይም ከዚያ በላይ** | አዎን/Yes | አዎን/Yes | አዎን/Yes | እንደ "F" ሆኖ የውጤት-ደረጃ የተሰጠው | ምንም ዳግም-ማስገባ/resubmission አልተፈቀደም |

ጥፋቶች (Offenses)፤ በአንድ የትምህርት አመት ውስጥ - በየእያንዳንዱ ኮርሶች - አጠቃላይ-ድምር ነው፤ እና ቆጠራው - በእያንዳንዱ የትምህርት ዓመት መጀመሪያ ላይ እንደገና ይጀምራል።

የጥሰቶች/offenses ልዩ-ምደባ የሆነው (ማለትም፤ ምን-ዓይነት ባህሪይ እንደ አነስተኛ-የሆነ/minor ወይም ከፍተኛ-የሆነ ጥፋት/major offense እንደሚወሰድ) በእያንዳንዱ ትምህርት ቤት ውስጥ በሚካሄድ አወሳሰን-አማካኝነት የሚወሰን-ነው። ሁሉንም-አሟጥጦ ያላካተተ - የጥፋቶች/offenses ምደባዎች - የምሳሌዎች ዝርዝር፣ እንደሚከተለው ነው:

- **አነስተኛ-የሆኑ ጥፋቶች/Minor Offenses**: ተገቢ-ያልሆነ ወይም ምንም-ጥሰቶች አለመኖር፣ የቤት/ክፍል ስራውን አነስተኛውን ክፍል ማጭበርበር፣ ባልተፈቀደ-ሁኔታ/impermissibly[34] የቤት/ክፍል ስራውን አነስተኛውን ክፍል ላይ አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ (AI) በመጠቀም፣ የቤት/ክፍል ስራውን አነስተኛውን ክፍል ላይ፣ ወይም በልምምድ እና የትግበራ ስራዎች ላይ መልሶችን መቅዳት/መኮረጅ።
- **ከፍተኛ-የሆኑ ጥፋቶች/Major Offenses**: የ'AI' ፕሮግራምን በመጠቀም - አጠቃላይ የቤት/የክፍል ስራው (assignment)ን አስመስሎ-መቅዳት፤ መልሶችን መኮረጅና ማመለስ ወይም በሁሉም-በአንድ የቤት/የክፍል ስራው (assignment) ውስጥ 'AI' ን መጠቀም፤ ወይም ፈተና፣ በፕሮጀክት፣ ወይም ዋና በሆነ የቤት/የክፍል ስራ (major assignment) ላይ ማጭበርበር።

---

33 ትምህርት ቤትውስጥ በ'SBT' ላይ ጥሰት/infraction በሚመዘገብ-ጊዜ፣ ያ መረጃ ወዲያውኑ ወደ ፓኖራማ (Panorama) ይገባል።

34 የDCPS ሠራተኞች - የ'Ed Tech Information & Resources SharePoint'ን፣ በመማሪያ-ክፍል ውስጥ 'AI'ን ለመጠቀም የበለጠ የመረጃ-ምንጮች/resourcesን ለመጠቀም - የ'DCPS Artificial Intelligence Toolkit'ን ጨምሮ - መጎብኘት ይችላሉ።

### E. በመቅረት/Absence-ምክንያት - መውደቅ

በማንኛውም ክፍል ውስጥ አስር (10) ያለምክንያት ፈቃድ-ሳያገኙ መቅረቶች - የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ከሰላሳ (30) በላይ - ፈቃድ-ያላገኙ መቅረቶች (unexcused absences)ን ሲጠራቀሙ፤ በዚያ ትምህርት "FA" (በመቅረት ምክንያት መውደቅ/Failure Due to Absences) የማግኘት አደጋ-ላይ መሆናቸውን-ለማሳወቅ፣ ልዩ-የሆነ ተቀባይነት-ካላገኘ በስተቀር - የመጀመሪያ የጽሁፍ ማስታወቂያ ይደርሳቸዋል።[35] በማንኛውም-ክፍል ውስጥ - አስራ አምስት (15) ፈቃድ-ያላገኙ መቅረቶች (unexcused absences) ያላቸው የሁለተኛ-ደረጃ ተማሪዎች፣ ከሰላሳ (30) በላይ ፈቃድ-ያላገኙ መቅረቶች (unexcused absences) ሲያጠራቅሙ፤ በዚያ ትምህርት "FA" (በመቅረት ምክንያት መውደቅ/Failure Due to Absences) የማግኘት ስጋት-ላይ መሆናቸውን የሚገልጽ፣ ተጨማሪ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ይደርሳቸዋል።[36]

በአንድ ሙሉ የትምህርት ዓመት ውስጥ - በኮርሱ፣ ከሰላሣ (30) ፈቃድ ያላገኘ መቅረቶች (unexcused absences) በላይ - ያጠራቀሙ የሁለተኛ-ደረጃ ተማሪዎች፤ በኮርሱ ክሬዲት የማጣት (loss of course credit) ሁኔታን ከሚያስከተልው ጋር፤ በዚያ ኮርስ የመውደቅ-የመጨረሻ የደረጃ ውጤትን (ማለትም፤ "F"ን) ያገኛሉ።[37]

### F. ይግባኝ-ማለት/አቤቱታ ማቅረብ (Appeals)

1. በመቅረት ምክንያት ለደረሰ መውደቅ - የይግባኝ-አቤቱታ ማቅረብ

ፈቃድ-ባላገኘ ከትምህርት-ገበታ መቅረቶች (unexcused absences) ምክንያት፤ ማንኛውም የመውደቅ የውጤት ደረጃ(ዎች) የተቀበለ ተማሪን በመወከል፤ የጽሁፍ-አቤቱታውን - በወላጅ፣ ቀደምት-የሆነ እንክብካቤ-ሰጪው፣ ወይም በተማሪ - ፋይል ሊደረግ ይችላል።[38] ይህ አቤቱታ በሚማሩበት ትምህርት ቤት ወደአለው ርዕሰ-መምህር ወይም የቻንስለሩ ተወካይ ወደሆኑት - የወደቁበትን የውጤት-ደረጃ(ዎች) ካገኙ - በአስር (10) ቀናቶች ውስጥ - መግባት አለበት።[39] ሁሉም አቤቱታዎች - ቤተሰቡ በሚመርጠው ግንኙነት-የማድረጊያ ቋንቋ - ተቀባይነት አለው።

ይህን-መሰል አቤቱታን ከተቀበሉ በኋላ፣ ርዕሰ-መምህሩ ወይም የቻንስለሩ ተወካይ - የአቤቱታዎች ፓኔል (Appeals Panel)ን የሚመርጡ እና ሁሉንም የጽሁፍ አቤቱታ መጠየቂያዎችን ወደ ፓኔሉ ሊቀመንበር በሦስት (3) የትምህርት-ቀናቶች ውስጥ አስተላልፈው-ይሰጣሉ።[40] ይህ የአቤቱታዎች ፓኔል (Appeals Panel) - ከሦስት (3) ያላነሱ አባላቶችን የያዘ መሆን ያለበት ሲሆን፣ ከሚከተሉት ውስጥ የሚመረጡትን - አንደኛው - ከምድብ/category (a) መሆን-አለበት:

a. በርዕሰ መምህሩ ወይም በቻንስለር ወኪሉ (Chancellor's designee) የተመደበ - የፓኔሉ ሊቀመንበር ሊሆን የሚችል-ሰው፤
b. የመመሪያ ካውንስለር/guidance counselor፤
c. የመምሪያው/department ሊቀመንበር፤
d. አስተማሪ፣ አቤቱታ-በቀረበበት ጉዳይ ውስጥ ከገባው አስተማሪ-ውጪ የሆነ፤
e. በትምህርት-ገበታ ላይ መገኘት (attendance) ላይ የሚሠራ-ሰው፣ ወይም
f. ከDCPS ማዕከላዊ አገልግሎቶች - የመጣ ወኪል።[41]

አስፈላጊ-ሆኖ ሲገኝ - ከሁለት (2) ያልበለጡ የይግባኝ ፓነል/Appeals Panel አባላቶችን - ለመተካት ይቻላል።[42]

የይግባኝ ፓነሉ (The Appeals Panel)፤ በርዕሰ-መምህሩ ወይም በቻንስለር ተወካይ ከተሾሙ-በኋላ፣ በአስር (10) የትምህርት ቀናት ውስጥ የችሎት-ተሰሚነት/hearing ማካሄድ አለበት።[43] ተማሪው፣ ወላጃቸው(ጆቻቸው)/አሳዳጊ(ዎች)፣ ወይም ወኪል-ለመሆን ስልጣን የተሰጠው ሰው - ተማሪውን ለመወከል በችሎት-ተሰሚነት/hearing ላይ ይቀርባሉ። ከእነዚህ ግለሰቦች መካከል-አንዱ፣ የተማሪውን ጉዳይ እንዲያቀርብ እና በተጠየቀ-ጊዜም - ለዚህ-ጉዳይ ጥያቄ የቀረበበትን አስተማሪን ጥያቄ-እንዲጠይቅ እና በፓናሉ የተሰጡ-ምክሮችን - በደንብ እንዲያውቁት ዕድል ይሰጣቸዋል።[44]

---

35 5-B DCMR § 2103.4.
36 5-B DCMR § 2103.5.
37 5-B DCMR § 2103.6.
38 5-B DCMR § 2103.7.
39 5-B DCMR § 2103.8.
40 5-B DCMR § 2103.9.
41 5-B DCMR § 2103.10.
42 5-B DCMR § 2103.11.
43 5-B DCMR § 2103.12.
44 5-B DCMR § 2103.13.

ሊቀ-መንበሩን ጨምሮ እያንዳንዱ የይግባኝ ፓናሊስቶች (appeals panelist) - እኩል ድምጽ ይኖራቸዋል። ሆኖም-ግን ሁለት (2) ድምጽ ሰጪ አባላቶች - ውሳኔ-ሊሰጡ ይችላሉ።[45] እኩል-የሆነ ድምጽ በሚሰጥበት-ጊዜ፣ በይግባኝ ፓነል (Appeals Panel) - የመጀመሪያው የውጤት-ደረጃ/initial grade እንዳልተደረገ ሆኖ ይቆጠራል።[46] የይግባኝ ፓነል (Appeals Panel) - የውሳኔ ሃሳቡን፣ ወዲያውኑ ለርዕሰ-መምህር ወይም ለቻንስለር ተወካይ የሚያስተላልፍ-ሲሆን፣ እርሱም ከፍትድ-ቤት ተሰሚነት (hearing) በኋላ - በአስር (10) የትምህርት ቀናት ውስጥ - የፓነል ውሳኔውን ይሰጣል።[47]

ተማሪው፣ ወላጃቸው(ጆቻቸው) ወይም ስልጣን-የተሰጠው ተወካይ፤ ውሳኔው በደረሰው በአስር (10) የትምህርት ቀናት ውስጥ - ለቻንስለር ኦፊሴላዊ የውጤት-አሰጣጥ የይግባኝ-አቤቱታ ተወካይ - በመፃፍ፣ በይግባኝ ፓኔሉ (Appeals Panel) ውሳኔ-ላይ አቤቱታ-ማቅረብ ይችላሉ።[48] በይግባኝ ፓኔሉ (Appeals Panel) ውሳኔ-ላይ - የዚህ ተወካይ የሚገኙበት አድራሻ - የሚካተት-ይሆናል። በይግባኝ ፓኔሉ (Appeals Panel)ን ውሳኔ-ላይ አቤቱታ ፋይል-በሚደረግ ጊዜ፤ ቻንስለር ኦፊሴላዊ የውጤት-አሰጣጥ የይግባኝ-አቤቱታ ተወካዩ - የገቡትን ሁሉንም ሰነዶች ዳግም-የሚመለከቱ እና በዚህ ጉዳይ ላይ የመጨረሻ አስተዳደራዊ ውሳኔ ይሰጣሉ።[49] በሁሉም የቀረቡ ማስረጃዎች ላይ ግምገማ-ከተካሄደ እና ከግምት-ውስጥ የሚገቡ-ነገሮችን ከተመለከቱ በኋላ፣ በአምስት (5) የትምህርት ቀናት ውስጥ፣ ይህ የጽሁፍ ውሳኔ ይሰጣል።[50] በይግባኝ ፓኔሉ (Appeals Panel)ን ውሳኔ-ላይ በቀረበው በዚህ የሁለተኛ-ደረጃ ባለው የይግባኝ-ጥያቄ ላይ፣ ጥያቄ-የቀረበበትን የውጤት-ደረጃ(ዎች)ን - ለምን መቀየር-እንዳለበት የማሳየት ሸክሙ - በተማሪው ወይም በወላጆቻቸው ላይ ይሆናል፤ እና ጥብቅ የማስረጃ ህጎች - በስራ-ላይ አይውሉም።[51]

2. ሌላ የውጤት-ደረጃ ላይ አቤቱታ-ማቅረብ (Grade Appeals)[52]

ወላጅ ወይም ተማሪ፤ ትክክል-ያልሆነ፣ አሳሳች ወይም የተማሪውን ግላዊነት (student's privacy) የሚጥስ-ነው ተብሎ የሚታመነውን - ትምህርታዊ መዝገቦችን፣ እንዲስተካከል የመጠየቅ መብት አላቸው። ለውጤት-ደረጃ ማስተካከያ - የመጀመሪያው-መጠየቂያ (initial request)፤ በጽሁፍ ለትምህርት ቤት ርዕሰ-መምህር - መግባት አለበት።

የትምህርት ቤቱ ርዕሰ-መምህር የመከራከርያ-ጥያቄው ለደረሰበት አስተማሪ፣ ወዲያውኑ በጽሁፍ ያሳውቃል እና አስተማሪው የተሰጠውን ውጤት ለማረጋገጥ ሁሉንም ተጨባጭ፣ ተዛማጅነት ያላቸው፣ ዝርዝር እና ቀን-ተጽፎበት የተመዘገቡትን - እንዲያቀርብ ይጠይቃል።[53] የይግባኝ-ጥያቄው በደረሰው በአስር (10) የትምህርት ቀናት ውስጥ፣ ርዕሰ-መምህሩ፣ የቀረቡትን መዝገቦች በሙሉ - ከተከራካሪው አካል ወይም ተወካዩ ጋር እና ከመምህሩ ጋር ተመልክቶ፣ ውሳኔ ይሰጣል። በዚህ የውጤት-ደረጃ የመከራከርያ-ጥያቄ ሂደትን በተከተለ-ሁኔታ - በማንኛውም የውጤት-ደረጃ ላይ ማስተካከያ-ከተደረገ፤ ርዕሰ-መምህሩ፣ ይህ ጥያቄ-ለቀረበበት አስተማሪ - ማስተካከያው ከመደረጉ በፊት፣ በጽሁፍ ማሳወቅ እና ማስተካከያው-የተደረገበትን ምክንያቶች በማካተት፣ ማሳወቅ-አለባቸው።[54]

---

45 5-B DCMR § 2103.14.
46 5-B DCMR § 2103.15.
47 5-B DCMR § 2103.16.
48 5-B DCMR § 2103.17.
49 5-B DCMR § 2103.18.
50 5-B DCMR § 2103.19.
51 5-B DCMR § 2103.19.
52 5-E DCMR § 2602 ከዚህ ሂደት ጋር ግንኙነት-ያለውን ደንቦች ያቀርባል።
53 በአሜሪካ የአስተማሪዎች ፌዴሬሽን እና በኮሎምቢያ ዲስትሪክት የህዝብ ትምህርት ቤቶች መካከል በዋሽንግተን የአስተማሪዎች ህብረት - Local #6/American Federation of Teachers and The District of Columbia Public Schools - መካከል የጋራ-ስምምነት፤ October 1, 2020 – September 30, 2023; Art. 19.1.1-.2, በዚህ-ላይ ይገኛል*t* dcps.dc.gov/page/washington-teachers-union-wtu.
54 በአሜሪካ የአስተማሪዎች ፌዴሬሽን እና በኮሎምቢያ ዲስትሪክት የህዝብ ትምህርት ቤቶች መካከል በዋሽንግተን የአስተማሪዎች ህብረት - Local #6/American Federation of Teachers and The District of Columbia Public Schools - መካከል የጋራ-ስምምነት፤ October 1, 2020 – September 30, 2023; Art. 19.1.2, *available at* dcps.dc.gov/page/washington-teachers-union-wtu.

ወላጅ ወይም ተማሪው - የር ዕሰ-መምህሩን ውሳኔ - ወደ ትምህርት ቤቱ -የትምህርት አሰጣጥ ጠቅላይ-ስራ አስኪያጅ[55] የጽሁፍ የይግባኝ-አቤቱታውን፣ የርዕሰ-መምህሩን ውሳኔ በተቀበሉበት በአስር (10) የቀን-መቁጠሪያ ቀናት ውስጥ፣ አቤቱታው ሊያስገቡ ይችላሉ።

ይግባኙ - ለትምህርት-አሰጣጥ የበላይ-ተቆጣጣሪ በሚደርሰው-ጊዜ፤

የትምህርት-አሰጣጥ የበላይ-ተቆጣጣሪው - ይግባኙ በደረሰው-ጊዜ - ይግባኙን ለመመልከት እና ሁሉንም የገቡትን ማስረጃዎች ከግምት-ውስጥ ለማስገባት እና የመጨረሻ ውሳኔውን በጽሁፍ ለማቅረብ፤ አስር (10) የትምህርት-ቀናት - ይኖረዋል። የሚከተሉትን - የክንውናዊ-ሂደት መመሪያዎች - በስራ-ላይ ይውላሉ:

- በጥያቄ ውስጥ ያለው የውጤት-ደረጃ(ዎች) ለምን-መቀየር እንዳለበት የማሳየት ሸክሙ፣ በተማሪው ወይም በወላጆቻቸው ላይ ይሆናል፤ እና
- ጥብቅ-የሆኑ የማስረጃ ህጎች ተፈጻሚነት አይኖራቸውም።

### G. የተማሪዎች ዝውውር/Transfer Students

ከሌላ የዲስትሪክት ትምህርት ቤት ወይም ቻርተር ትምህርት ቤት - ወደ DCPS የሚዘዋወሩ ተማሪዎች፤ የትምህርት ማስረጃዎቻቸው (transcripts) የሚገመገሙ እና፣ ለአሁኑ ተርም/term ተገቢ-ወደሆኑት ኮርሶች ይመደባሉ።[56] ወደ ትምህርት ቤቱ እየገባ ያለው ተማሪ -

የትምህርት ማስረጃ (transcript)ን ማቅረብ ካልቻለ፣ ተመዝግቦ-በሚገባበት ጊዜ፣ የተማሪውን ቀደም-ሲል የነበረውን መዝገብ - በፊት ከነበረበት ትምህርት ቤት፣ እንዲሰጠው-የመጠየቅ ኃላፊነት፣ የተማሪው አዲሱ-ትምህርት ቤት ነው። ተማሪው፣ በቀድሞው ትምህርት ቤት ውስጥ - ተመዝግቦ ወደነበረበት ኮርስ ከገባ፣ ከዚህ ቀደም ያስመዘገበው ውጤቶች ወደዚህ-መተላለፍ አለበት፣ እና ተማሪው በትምህርቱ እድገት-እያመጣ እንዲቀጥል ሊፈቀድለት ይገባል።

በመጀመሪያ የተርም/term አጋማሽ-ወቅት - ተማሪው ከዚህ-ቀደም በተመዘገቡበት ኮርስ ውስጥ ካልገባ፤ በኮርሱ ውስጥ ሊመዘገቡ የሚገባቸው እና በዚያ-ተርም/term ውስጥ ሳያጠናቅቁ-ያመለጣቸውን ስራ - እስከተርሙ/term መጨረሻ-ድረስ - አካክሰው/make up-አድርገው እንዲሰሩ ዕድል ይሰጣቸዋል።

- ተማሪው፤ ኮርሱን በሚጠይቀው - በመጀመሪያዎቹ አስር (10) የትምህርት ቀናት ውስጥ - በኮርስ ውስጥ ከገባ፣ Section IV.C.6 (Makeup and Late Work) ላይ እንደተገለፀው - ሁሉም የዘገየ ስራ (late work) መደበኛ-የሆኑ የጊዜ-ገደቦች - በስራ-ላይ ይውላሉ።
- ተማሪው፣ ከአስረኛው የኮርሱ ስብሰባ በኋላ ወደ ኮርስ ከገባ፣ አስተማሪዎቻቸው - ወደ ኮርሱ በገቡበት ጊዜ እና በኮርስ ስራው ባለው ብቃት ላይ በመመስረት ለማካካሻ የቤት/ክፍል ስራዎቻቸው (makeup assignments) - የየግል የጊዜ-ገደቦችን ያዘጋጃሉ። የማካካሻ የቤት/ክፍል ስራዎቻቸው (makeup assignments) ለማስገባት - መደበኛ-የሆነውን ወይም የየግል የጊዜ-ገደቦቻቸው - ሳያስገቡ-ካመለጧቸው፤ በSection IV.C.6 (Makeup and Late Work).በተገለጸው-መሠረት - የውጤት መቀነሻ/grade reduction ደብዳቤን ያገኛሉ።

አንድ ተማሪ፣ ቀደም-ሲል - በተርሙ/term ሁለተኛው አጋማሽ ላይ ባልተመዘገቡበት ኮርስ ውስጥ ከገባ፣ እንደ 'ዘግይቶ የገባ/Late Entry' ይወሰዳል። እነዚህ ተማሪዎች - በኮርሱ ውስጥ ሊመዘገቡ የሚችሉ እና በዚያ-ተርም/term ውስጥ ሳያጠናቅቁ-ያመለጣቸውን ስራ - እስከሚቀጥለው ተርም/term ድረስ አካክሰው/make up-አድርገው እንዲሰሩ ዕድል ይሰጣቸዋል። አሁን-ባለው ተርም/term መጨረሻ ላይ - ሁሉም የኮርሱ-ስራ/courseworkን ካላጠናቀቁ፣ በሪፖርት ካርዳቸው ላይ - "L" (ዘግይቶ የገባ/Late Entry)ን ያገኛሉ። የኮርሱ-ስራ/coursework - በሚቀጥለው የተርም/term መጨረሻ-ላይ ከተጠናቀቀ፤ "L" ይወገድ እና፣ ተማሪው - ተገቢ-የሆነውን ውጤት ያገኛል።

ተማሪው፣ ለሙሉ ኮርስ ካያልተመዘገበ-ከሆነ፣ ነገር-ግን የጊዜ-ሰሌዳ በተያዘለት ክፍል-ውስጥ - ቢያንስ 25% የተሳተፈ-ከሆነ፣ በተሸፈነው ትምህርት ውስጥ - የላቀ-ችሎታን እንዲያሳይ እና በብቃት ላይ በተመሠረተ ግምገማ አማካኝነት - ክሬዲት እንዲያገኝ እድል ሊሰጣቸው ይገባል።

---

55 በዚህ-ላይ በመመልከት dcps.dc.gov/page/instructional-superintendents የሚመለከታቸውን - የትምህርት-አሰጣጥ የበላይ-ተቆጣጣሪን ለመለየት እና የሚገኙበትን -አድራሻ ለማግኘት ተመልከቱ።

56 ለመጪው የተማሪዎች ዝውውር እና የክሬዲት ዝውውር - ተጨማሪ መረጃዎችን ለማግኘት፤ እባካችሁ በዚህ-ላይ ተመልከቱ dcps.dc.gov/publication/transfer-of-credit-policy.

## V. ፖሊሲውን ለማስፈጸም የሚፈለጉ መስፈርቶች

ሁሉም የDCPS ተቀጣሪ-ሠራተኞች፤ በዚህ በተቀረጸው ፖሊሲ መስፈርቶች መገዛት ያስፈልጋቸዋል። አፈፃጸሙን ለመደገፍ፣ የሚፈለጉትን እንቅስቃሴዎች እና የጊዜ-አቀማመጥን - በዚህ ፖሊሲ ውስጥ ባለው ዓመታዊ አሰራር መሠረት፤ ሁሉም ሠራተኞች እንዲያውቁት፣ የሁለተኛ-ደረጃ ትምህርት ቤት ርዕሰ መምህራኖች ማድረግ የሚጠበቅባቸው ነው።

የዚህ ፖሊሲ አፈፃፀም፤ በመደበኛ የመረጃ ስብስብ (data) ምልከታዎች፣ የመዝገብ ናሙናዎች፣ ከስር ያሉ ሰነዶች ላይ ምልከታ በማድረግ፣ እና ቦታዎችን መጎብኘት - እንደየ-አስፈላጊነቱ - እነዚህን ሁሉ ያካተተውን፣ በማዕከላዊ የበላይ ክትትል ሂደት አማካኝነት ተጠናክሮ ይካሄዳል። ይህ ማዕቀፍ (framework)፣ ቀጣይነት ያለው ማሻሻያዎችን እና አለመገዛትን-የሚከላከል ዘዴን፣ DCPS መገንባቱን ያረጋግጣል።

DCPS፤ እያንዳንዱን ተማሪ፤ በፍህታዊ-እኩልነት፣ የላቀ-በላጭነት ባለው አሰራር፣ በግልጽነት፣ እና ተጠያቂነት ባለው-ሁኔታ ለማገልገል - ቁርጠኝነቱን ያሳያል። ስለዚህ ፖሊሲ በተመለከተ የሚኖሩ ጥያቄዎች ወይም ስጋቶችን፣ ወደ 'Office of SEAD Strategy' ወይም የሃቀኝነት ቢሮ (the Office of Integrity)፤ መቅረብ አለባቸው። ስለዚህ ትዕዛዝ-መስጫ፣ ማንኛውንም ስጋቶች ወይም ጥሰቶችን ለማሳወቅ፤ የሃቀኝነት ሹሙ ዋና የሆነው (Office of Integrity)ን ለማነጋገር፤ የኦንላይን-መምሪያ (Online Referral) ቅጽን[57] በመሙላት ወይም ወደ dcps.cio@k12.dc.gov ኢሜል መላክ።

---

[57] *Available at* dcps.dc.gov/page/office-integrity.